በኮሮናቫይረስ (ኮቪድ-19) የተያዘች እናት ልጇን ማጥባት ትችላለች?


አዎ! ከወሊድ በኋላ አንዲት እናት በኮሮናቫይረስ (ኮቪድ-19) ብትያዝም ሕጻን ልጇን መንካትም ማጥባትም ትችላለች።

ነገር ግን የሚከተሉትን ጥንቃቄዎች ማድረግ አለባት።

- አካባቢዋን ማጽዳት
- ሕጻኑን ከመንካቷ በፊት እና በኋላ እጆቿን በሳሙና እና በውሃ መታጠብ
- ሕጻኑን በምታጠባበት ወይም በምትመግብበት ጊዜ አፍና አፍንጫዋን መሸፈን

እናቲቱ በሽታው ከጸናባት ሕጻኑን ከእናቲቱ በመለየት አማራጭ የሕጻናት ምግብን እንዲመገብ መደረግ አለበት።

ትክክለኛ የእጅ አስተጣጠብ ቅደም ተከተል





የኮሮናቫይረስ በሽታን (ኮቪድ-19) ለመከላከል ለነፍሰጡር ሴቶች እና ለእናቶች ጠቃሚ መረጃዎች

ለበለጠ መረጃ
በነፃ የስልክ መስመሮች
8335 ወይም 952
ላይ ይደውሉ



ነፍሰጡር ሴቶች ከእርግዝና ጋር በተያያዘ በሽታን የመቋቋም ብቃታቸው ከሌሎች እናቶች ሊቀንስ ስለሚችል ከመውለዳቸው በፊት፣ በወሊድ ወቅትና ከወሊድ በኋላ በኮሮናቫይረስ በሽታ (ኮቪድ-19) እንዳይያዙ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድርግ ይኖርባቸዋል።

ነፍሰጡር ከሆንሽ

- መደበኛ የሆነ የቅድመ ወሊድ ክትትልሽን አታቋርጪ
- እጅሽን በውሃና በሳሙና አዘውትረሽ ታጠቢ ወይም አልኮል ባለዉ የጀርም ማጽጃ /ሳኒታይዘር/እጅሽን አፅጂ
- እጅሽን ሳትታጠቢ አይኖችሽን፣ አፍሽን እና አፍንጫሽን አትንኪ
- ከማንኛውም ሰው ቢያንስ ሁለት ሜትር ርቀትሽን ጠብቂ
- የህክምና እርዳታ ሰጪ ቡድን እስኪደርስ እራስሽን ከሌሎች በመለየት በአንድ ክፍል ዉስጥ ለብቻሽ ቆዪ
- ስታስነጥሺ ወይም ሲያስልሽ አፍሽንና አፍንጫሽን በሶፍት ወይም በክርንሽ ሸፍኚ
- የተጠቀምሽበትን ሶፍት ክዳን ባለው ቆሻሻ ማጠራቀሚያ ውስጥ አስወግጂ

የጆኮሮናቫይረስ በሽታ ምልክቶችን ካስተዋልሽ ባስቸኳይ በነጻ የስልክ መስመር 8335 ወይም 952 በመደወል የሕክምና እርዳታ ጠይቂ

የኮሮናቫይረስ በሽታ ምልክቶች



ትኩሳት



ሳል



የትንፋሽ ማጠር፣ ለመተንፈስ መቸገር እና የጉሮሮ ህመም

በሽታው ሲባባስ ደግሞ የሳንባ ምች እና የኩላሊት ስራ ማቆም እና ሞትን ሊያስከትል ይችላል።